የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፶፬
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 54
ADDIS ABABA-8th May, 2003.

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ... ገጽ ፪ሺ፩፻፸፪

CONTENTS

Proclamation No. 334/2003
Authentication and Registration of Document Proclamtion ........................................ Page 2172

### አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭
### ስለሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ የወጣ አዋጅ

የሰነድ ማረጋገጥ ሥራ እምነት የሚጣልበት ማስረጃ የሚያስገኝና በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰዎችና በድርጅቶች መካከል የሚደረጉ የውልና ሌሎች ግንኙነቶችን የሚያመቻች በመሆኑ፣

የሰነዶች ምዝገባ ሥራ ሰነዶች ምንጊዜም ሲፈለጉ እንዲገኙ አስተማማኝ ሁኔታ የሚፈጥር በመሆኑ፣

የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራ በአገሪቱ ውስጥ በፍርድ ቤቶችና በሌሎችም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ልምድን መሠረት በማድረግ ሲካሄድ የቆየ በመሆኑና የዚህን ሥራ ተግባራትና ሥራውን የሚያከናውኑ ተቋማትን ሥልጣንና ተግባር የሚወስን አንድ ወጥ የፌዴራል ሕግ ባለመኖሩ፣

የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚነት በሚኖረው አንድ ወጥ የፌዴራል ሕግ ቢመራ በዜጎች መካከል የሚከናወኑ የንግድና ሌሎችንም የኢኮኖሚ ግንኙነቶች በማቀላጠፍ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፣

የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራ የሚያከናወኑ ተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት በሕግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

#### ክፍል ፩
#### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ፫፻፴፬/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

### *PROCLAMATION NO. 334/2003*
### *PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE AUTHENTICATION AND REGISTRATION OF DOCUMENTS*

WHEREAS, Authentication of documents provide a reliable means of evidence and thus facilitate contractual and other relations between persons and organizations both at the domestic and international levels;

WHEREAS, registration of documents ensures the availability of documents whenever they are required;

WHEREAS, the functions of authentication and registration of documents have been carried out in the country by courts and other public offices based on practice and that there was no relevant Federal legislation which determines the scope of the work and the powers and duties of organs involved in the provision of notarial services;

WHEREAS, applying uniform federal legislation on authontication and registration of documents through out the country have positive impact on the flixibility of the Trade and other business relations between the citizens.

WHEREAS, it is necessary to define by law the powers and duties of institutions that carry out the functions of authentication and registration of documents;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

#### PART 1
#### General

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Authentication and Registration of Documents Proclamation No. 334/2003."

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3·40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፩· "ሰነድ ማረጋገጥ" ማለት አዲስ ሰነድ በአዘጋጁ ወይም ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ሲፈረም ማየትና ይኸው መፈጸሙን በማረጋገጥ በሰነዱ ላይ መፈረምና ማኅተም ማድረግ ፤ ወይም አስቀድሞ በተፈረመ ሰነድ ላይ የሚገኝ ፊርማንና ወይም ማኅተምን በቃለ መሐላ ፤ ወይም በናሙና ፊርማና ወይም ማኅተም በትክክል መሆኑን በማረጋገጥ በሰነዱ ላይ መፈረምና ማህተም ፤ ማድረግ ነው ።

፪· "ሰነድ" ማለት ማናቸውም ውል ፤ ኑዛዜ ፤ የውክልና ሥልጣን መስጫ ሰነድ ፤ ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ ቋንቋ ጽሑፎችን ለመተርጎም ፈቃድ በተሰጠው ሰው የተተረጎመ ጽሑፍ ፤ የሰነድ ቅጂ ወይም ግልባጭ ፤ የማኅበራት መመሥረቻ ጽሑፍ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ፤ ቃለ ጉባዔ ወይም ማናቸውም በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገብ የቀረበ ጽሑፍ ነው ።

፫· "ሰነድ መመዝገብ" ማለት አንድ የተረጋገጠ ሰነድን ለዚሁ በተዘጋጀ መዝገብ መለያ ቁጥር በመስጠት መመዝገብና ማስቀመጥ ፤ ወይም በሕግ መሠረት በሰነድ አረጋጋጭ ባለሥልጣን እንዲቀመጥ የተባለ ሰነድን ተቀብሎ መመዝገብና ማስቀመጥ ነው ።

፬· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው ።

፭· "ሰነድ አረጋጋጭ" ማለት ሰነድ ለማረጋገጥ በአግባቡ ሥልጣን የተሰጠው የሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት ሠራተኛ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፮ ከተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች የማናቸውም መሥሪያ ቤት ሠራተኛ ነው ።

፮· "የከተማ መስተዳድር" ወይም "የከተማ መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት እንደሁኔታው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ወይም ምክር ቤት ወይም የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ወይም ምክር ቤት ነው ።

፫· <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ፤

፩· በክልል መስተዳድሮች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ፤

፪· በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች በዚህ አዋጅ ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ፤

፫· በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤ በውጭ አገር በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች ፤

፬· በመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች እና

፭· በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች በሚረጋገጡና በሚመዘገቡ ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ።

## ክፍል ፪
## የሰነድ ማረጋጋጥ ተግባራትና የአረጋገጩ ግዴታዎች

፬· <u>የሰነድ ማረጋገጥ ተግባራት</u>

የሰነድ ማረጋገጥ ተግባራት የሚከተሉትን ያጠቃልላል ።

፩· ሰነዶችን ማረጋገጥና መመዝገብ ፤

፪· የሰነድ ቅጂዎችን ከዋናው ጋር በማመሳከር ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥና መመዝገብ ፤

፫· ቃለ መሐላና በቃለ መሐላ የሚሰጡ ማረጋገጫዎችን መቀበልና መመዝገብ ፤

፬· ባለጉዳዮች ሲጠይቁ እንዳስፈላጊነቱ የፊርማ እና/ወይም የማኅተም ናሙና መያዝ ፤

፭· ለመረጋገጥ በሚቀርቡ ሰነዶች ላይ የሚፈርሙ ወይም የፈረሙ ሰዎችን ችሎታ ፤ መብትና ሥልጣን ማረጋገጥ ፤

፮· ለመረጋገጥ የሚቀርቡ ሰነዶችን ሕጋዊነት ማረጋገጥ ፤

1) "to authenticate a document" means to witness the signing of a new document by the person who has prepared such document or the person it concern and, after ascertaining that this formality is fulfilled, to sign and affix a seal on the document, or to sign and affix a seal on an already signed document by ascertaining its authenticity through an affidavit or specimen signature and/or seal;
2) "Document" means a contract, will, power of attorney, a document translated from one language into another by a licensed translator, copy of a document, memorandum or articles of association, minutes or any written matter submitted for authentication and registration;
3) "to register a document" means to register and authenticated document by marking it with an identification number, in a register prepared for the purpose and to deposit the same document, or to register and deposit a document which is required by law to be deposited with a notary;
4) "Person" means a physical or legal person;
5) "Notary" means the Federal Notary Office or an employee of the office or of any of those institutions mentioned under Article 26, duly authorized to authentication documents;
6) "City Government" means either the City Government of Addis Ababa or the City Council of Dire Dawa, as the case may be;

3. *Scope of Application*

This Proclamation shall apply to documents authenticted and registered by:

1) organs of the Regional Government authorized by respective Regional laws.
2) organs of the Addis Ababa and Dire Dawa City Governments authorized under this Proclamation;
3) the Ministry of Foreign Affairs, Ethiopian Embassies and Consular Office;
4) Commanders of divisions of the defence force; and
5) heads of federal prisons.

## *Part 2*
## *NOTARIAL ACTIVITIES AND DUTIES OF THE NOTARY*

4. *Notarial Activities*

Notarial activities include the following:

1) to authenticate and register documents;
2) to verify copies of documents against their originals and register same;
3) to administer oath and receive affidavits and register same;
4) to keep custody of specimen of signatures and/ or seal upon request by those concerned;
5) to ascertain the capacity, right and authority of persons who are about to sign or who have signed documents submitted for authentication;
6) to ascertain the legality of documents submitted for authentication;

፯· በሕግ የባለቤትነት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ በሚደረጉ ውሎች ፣
   ሀ) የንብረት አስተላላፊውን ባለመብትነት፣ እና
   ለ) ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ያልታገደ መሆኑን ማረጋገጥ ፣
፰· ስለተረጋገጡና ስለተመዘገቡ ሰነዶች ሥልጣን ባለው ወይንም አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ ማስረጃ መስጠት፣
፱· ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል ።

፭· <u>መረጋገጥና መመዝገብ ያለባቸው ሰነዶች</u>
፩· የሚከተሉት ሰነዶች በዚህ ሕግ መሠረት ካልተረጋገጡና ካልተመዘገቡ ሕጋዊ ውጤት አይኖራቸውም ።
   ሀ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት መረጋገጥና መመዝገብ ያለባቸው ሰነዶች ፣
   ለ) የውክልና ሥልጣን መስጫ ሰነዶች ፣
   ሐ) የንግድና ሌሎች ማኅበራት መመሥረቻ ጽሑፎችና፣ መተዳደሪያ ድንቦች እና ማሻሻያዎቻቸው ፣
፪· ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ሰነዶች ውጭ ሌሎች ሰነዶች እንዲረጋገጡላቸውና እንዲመዘገቡላቸው ባለጉዳዮች ሲጠይቁ ሰነድ አረጋገጩ እነዚህን ሰነዶች ያረጋግጣል ፣ ይመዘግባል ።

፮· <u>ክልከላ</u>
፩· አንድ ሰነድ አረጋጋጭ ፣
   ሀ) የራሱን ፣ የባለቤቱን ፣ የወላጆቹን ወይም የተወላጆቹን ፣ የወንድም ወይም የእህቱን ፣ የሚስት ወይም የባል ወላጆችንና እንዲሁም የሚስት ወይም የባል ወንድም እህትን ሰነድ ፣
   ለ) ራሱ ወኪል ወይም እንደራሴ የሆነለትን ሰው ሰነድ ማረጋገጥ አይችልም ።
፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ሰነዱ በሌላ ሰነድ አረጋጋጭ ይረጋገጣል ።
፫· እንዲሁም በሕግ እንዲሟሉ የተጠየቁ ሁኔታዎች ካልተሟሉ ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ የማረጋገጥ አገልግሎት አይሰጥም ።

፯· <u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>
፩· አንድ ሰነድ አረጋጋጭ በዚህ ሕግ መሠረት መስጠት ያለበትን አገልግሎት ቢከለከል ወይም ሕጉን በመተላለፍ አገልግሎት ቢሰጥ ማንኛውም ቅሬታ ያለው ሰው የሰነድ አረጋጋጩ የበላይ ለሆነው አካል በ፲፭ ቀን ውስጥ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል ።
፪· ባለ ጉዳዩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ካለው ወይም አቤቱታው ከቀረበለት ቀን ጀምሮ በ፴ /ሰላሳ/ ቀን ውስጥ ውሳኔ ካላገኘ ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል ።

፰· <u>የመተባበር ግዴታ</u>
አንድ ሰነድ አረጋጋጭ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ ሰነድ ወይም መረጃ ሲጠይቅ ፣ ማንኛውም ሰው የተጠየቀውን ሰነድ ወይም መረጃ በመስጠት ወይም በማቅረብ መተባበር አለበት ።

፱· <u>ሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ</u>
ማንኛውም ሰነደ አረጋጋጭ ፣
፩· በፍርድ ቤት ወይም በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ካልታዘዘ በቀር በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገባውን መረጃ ለሌላ ፫ኛ ወገን አሳልፎ አይሰጥም ።
፪· በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ነገር በምስጢር ይይዛል ።

## <u>ክፍል ፫</u>
## <u>ሰነድ የማረጋገጥ ሥርዓት</u>

፲· <u>አዲስ ሰነድ ስለማረጋገጥ</u>
፩· ሰነድ አረጋጋጩ አንድ ሰነድ እንዲረጋጋጥ ሲቀርብለት፣ ሰነዱን ለመፈረም የቀረበው ሰው ስሙና አድራሻው በሰነዱ ላይ የተጠቀሰው ሰው መሆኑን በማስረጃ አመሳክሮ ሰነዱን ያረጋግጣል ።



7) to ascertain with respect to contracts made to transfer properties for which title certificates are issued under the law:
   (a) the right of the transferor to transfer the property; and
   (b) that the property is not Mortgaged or pledged or that such property is not attached by a court order.
8) to provide information upon request by authoratative or approprate organ about authenticated and registered documents.
9) other simaliar activities.

5. *Documents that Must be Authenticated and Registered*
1) The following documents shall not have legal effect unless they are authenticated and registered:
   (a) documents that must be authenticated and registered in accordance with the appropriate law;
   (b) power of attorney;
   (c) memorandum and articles of association of business organizations, statutes of associations, and amendments thereof.
2) The Notary shall authenticate and register documents other than those mentioned above, if requested by the concerned parties.

6. *Prohibition*
1) A notary shall not authenticate:
   (a) his own documents and those of his relatives by consanguinity or affinity up to the second degree;
   (b) the document of a person for whom the notary is acting as agent or representative;
2) in the case of Article (1) the document shall be authenticated by another notary
3) The notary shall not give any notarial service unless the requirements of the law are satisfied;

7. *Right to Petition*
1) Any aggrieved person may submit a petition to the superior organ of the notary within 15 days where the notary refuses to give service that he must under the law, or gives service in violation of the law;
2) Where the person who has submitted a petition under Sub-Article (1) of this Article is not satisfied with the decision rendered or where no decision is rendered within 30 days from the date of submission of the petition he may bring an action in a court of law.

8. *Duty to Cooperate*
Any person required by a notary to give a document or information necessary for the notary's activities shall cooperate by producing the required document or by providing the required information.

9. Duty of Secrecy
A notary shall:
1) not give to third party information, which comes into his possession in the course of performing his duties unless ordered by a court or by a body empowered by law.
2) keep secret anything which he happens to know in the course of performing his duties.

## *PART 3*
## *PROCEDURE OF AUTHENTICATION*

10. *Authentication of a New Document*
1) Where a new document is submitted for authentication, the notary shall authenticate the document after having ascertained by means of evidence that the name address of the person who is about to sign the document is the same as the name and address on the document;

፪· ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ ሲያረጋግጥ ፣ አግባብ ባላቸው ሕጎች የተደነገገውን መከተል አለበት ።

፲፩· አስቀድሞ ስለተፈረሙ ሰነዶች

፩· ሰነድ አረጋጋጩ አስቀድሞ የተፈረመ ሰነድ እንዲረጋገጥ ሲቀርብለት ፣ በሰነዱ ላይ የሰፈረው ፊርማ ሰነዱን አስቀድሞ የፈረመው ሰው ፊርማ መሆኑን ወይም በሰነዱ ላይ የሚገኘው ማኅተም ትክክለኛው ማኅተም መሆኑን ያረጋግጣል ።

፪· የቀረበው ሰነድ በሌላ ሰነድ አረጋጋጭ የተረጋጋጠ ከሆነ በሰነዱ ላይ የሚገኘው ፊርማና ማኅተም የተባለው ሰነድ አረጋጋጭ ፊርማና ማኅተም መሆኑን ያረጋግጣል።

፲፪· ስለሰነድ ግልባጭ ወይም ኮፒ

፩· የአንድ ሰነድ ግልባጭ ወይም ኮፒ እንዲረጋገጥ ሲቀርብለት ፣ ሰነድ አረጋጋጩ ወይም የኮፒው ይዘት ከዋናው ሰነድ ይዘት ጋር እንዲሁም በግልባጩ ወይም በኮፒው ላይ ያለው ፊርማ ወይም ማኅተም በዋናው ሰነድ ላይ ካለው ፊርማና ወይም ማኅተም ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን በማመሳከር ሰነዱን ያረጋግጣል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተረጋገጠ የአንድ ሰነድ ግልባጭ የዋናውን ሰነድ ያህል የማስረጃነት ዋጋ ይኖረዋል ።

፲፫· የሰነዶችን ሕጋዊነት ስለማረጋገጥ

፩· ሰነድ አረጋጋጩ ሰነድ ከማረጋገጡና ከመመዝገቡ በፊት የሰነዱ ይዘት ሕግንና መልካም ጠባይን የማይቃረን መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

፪· ሰነድ አረጋጋጩ የአንድን ሰነድ ሕጋዊነት ከማረጋገጥ አልፎ የሰነዱን ይዘት የመለወጥ ወይም የማስለወጥ ሥልጣን የለውም ።

፲፬· የሰነድ ፈራሚዎችን ችሎታና ሥልጣን ስለማረጋገጥ

፩· ሰነድ አረጋጋጩ አንድን ሰነድ ከማረጋገጡ በፊት የፈራሚውን የመፈረም መብት ወይም ሥልጣን ማረጋገጥ አለበት።

፪· አንድ ሰነድ ፈራሚ የሕግ ችሎታ ያለው መሆኑ አጠራጣሪ ሲሆን ሰነድ አረጋጋጩ የፈራሚውን የሕግ ችሎታ ተገቢ በመሰለው መንገድ ማጣራት ይችላል ።

፲፭· የአንዳንድ ንብረቶችንና የባለንብረቱን ሁኔታ ስለማረጋገጥ

በሕግ የባለቤትነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸውን ንብረቶች ለማስተላለፍ የሚዘጋጁ ሰነዶች ከመረጋገጣቸው በፊት ሰነድ አረጋጋጩ ፣

፩· ንብረት አስተላላፊው አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ያለው መሆኑን ፣

፪· ንብረቱ በመያዣነት ያልተሰጠ ወይም በፍርድ ቤት ያልታገደ መሆኑን ፣

፫· ሰነዱን የሚፈረመው ሰው ሰነዱን ለመፈረም ከውል ወይም ከሕግ የመነጨ ሥልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

፲፮· ቃለ መሐላ ስለመቀበልና የምስክር ቃል ስለመስማት

፩· አንድ ሰው የአንድን ሰነድ ይዘት ትክክለኛነት በሰነድ አረጋጋጩ ፊት ቀርቦ በቃለ መሐላ ማረጋገጥ ይችላል ። ሰነድ አረጋጋጩም የተባለው ሰው በፊት ቀርቦ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ቃለ መሐላ መፈፀሙን በሰነዱ ላይ ይገልጻል ።

፪· አንድ ሰነድ አረጋጋጭ በፍርድ ቤት ሲታዘዝ የአንድን ሰው የምስክርነት ቃል ይቀበላል ።

፫· ሰነድ አረጋጋጩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የምስክርነት ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ምስክሩ ቃሉን የሰጠው በገዛ ፈቃዱ መሆኑን የምስክርነት ቃሉ በሰፈረበት ሰነድ ላይ ገልጾ ይፈርምበታል ማኅተሙንም ያትምበታል ።



2) The notary shall comply with the provision of the relevant law when he authenticates a document.

*11. Documents Already Signed*

1) Where a document which is alyready signed is submitted for authentication the notary shall authenticate such document by ascertaining that the signature on the document is that of the person who has signed it or that the seal on the document is genuine.

2) Where the document submitted for authentication is already authenticated by another notary, the notary shall authenticate the document by verifying that the signature and seal on the document is the signature and seal of the said notary.

*12. Copies of Documents*

1) Where a copy of a document is submitted for authentication, the notary shall authenticate the document by ascertianing that the contents of the copy are the same as those of the original document and that the signature and/or seal on the copy is the same as the signature and/or seal on the original document;

2) A copy of a document authenticated under Sub-Article (1) of this Article shall have the same probatory value as that of the original document.

*13. Ascertaining the Legality of Documents*

1) A notary shall, before authenticating and registering a document, ascertain that its contents are not illegal or immoral;

2) Apart from ascertaining it's legality, a notary shall not have power to change or cause to be changed the contents of a document submitted for authentication.

*14. Ascertaing the Capacity and Authority of Signatories of a Document*

1) The notary shall, before authenticating a document, make shure that the person who has signed or is about to sign the document has the right or authority to sign it;

2) Where it is doubtful that the person who has signed or is about to sign a document has capacity to do so the notary shall make the necessary investigation in a way he thinks proper to find out whether or not the signatory has capacity to sign.

*15. Ascertaining the Ownership and Other Conditions of Certain Properties*

Before authenticating documents relating to the transfer of properties for which title certificates are issued under the law, the notary shall ascertain that:

1) the transferor of the property has title certificate for the property in accordance with the relevant law;

2) the property is not mortgaged or pledged or is not attached by a court order;

3) the person who has signed or is about to sign the document has the right or authority, legal or contractual, to sign the document.

*16. Administration of Oath and Hearing of Witnesses*

1) A person may declare the truth of the contents of a document under oath before a notary. In such a case the notary shall state on the document that the said person has been sworn by him before he made the declaration;

2) A notary shall take the testimony of a witness where he is ordered by a court;

3) Where the notary takes the testimony of a witness under Sub-Article (2) of this Article, he shall state on the document that the witness give his testimony in his free will. The notary shall also sign the document and affix his seal thereon.

፲፯· ሞዴል ሰነዶችን ስለማዘጋጀት

፩· ሰነድ አረጋጋጩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ለተመለከቱትና እንደአስፈላጊነቱ ለሌሎች ሰነዶችም ሞዴል ማዘጋጀት ይችላል ።

፪· ሰነድ አረጋጋጩ ባዘጋጀው ሞዴል ሰነድ ለመጠቀም የሚፈልግ ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰነውን ዋጋ በመክፈል ሞዴል ሰነዱን ማግኘት ይችላል ።

፲፰· ሰነዶችን ስለመመዝገብና ስለማስቀመጥ

፩· ሰነድ አረጋጋጩ የሚያረጋግጣቸውን ሰነዶች ይመዘግባል ። ለእያንዳንዱ ሰነድ አንድ ግልባጭ በጽሕፈት ቤቱ ያስቀምጣል ።

፪· አንድ ሰነድ በሰነድ አረጋጋጭ እጅ እንዲቀመጥ በሕግ የተደነገገ ከሆነ ሰነድ አረጋጋጩ እንዲህ ያለው ሰነድ ሲቀርብለት ተቀብሎ ይመዘግባል ፣ ያስቀምጣል ።

፫· ሰነድ አረጋጋጩ በእጁ የሚገኝ አንድ የሰነድ ግልባጭ ወይም አንድ ሰነድ በእጁ ስለመኖሩ ጉዳዩ በሚመለከተው ሰው ማስረጃ ሲጠይቅ ፣ ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ግልባጩን ወይም ማስረጃውን ይሰጣል ።

ክፍል ፬

ስለሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ

ጽሕፈት ቤቶች

ንዑስ ክፍል አንድ

የክልል የሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት

፲፱· አደረጃጀት

፩· የክልል መስተዳድሮች ይህን አዋጅ የሚያስፈጽሙ የሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ ሊያደራጁ ይችላሉ ።

፪· ዝርዝሩን እንደየአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታ በራሳቸው ይወስናሉ ።

ንዑስ ክፍል ሁለት

የአዲስ አበባና የድሬዳዋ የሰነድ ማረጋገጫና ምዝገባ ጽሕፈት ቤት

፳· የጽሕፈት ቤቱ መቋቋም

፩· የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተሞች እያንዳንዳቸው አንድ ጽሕፈት ቤት ይኖራቸዋል ።

፪· የፌዴራሉ የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ሥራ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ በሚቋቋሙት ጽሕፈት ቤቶች ይከናወናል ።

፳፩· የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፣

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተዘረዘሩት ተግባራት ያከናወናል፣

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት እንደ አስፈላጊነቱ ሞዴል ሰነዶችን ያዘጋጃል ፣

፫· ውል ይዋዋል ፣

፬· ንብረት ይይዛል ፣ ያስተላልፋል ፣

፭· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ተግባር ሁሉ ይፈጽማል ።

፳፪· አደረጃጀት

ጽሕፈት ቤቱ በከተማው መስተዳድር ምክር ቤት የሚሾም አንድ የጽሕፈት ቤት ኃላፊ ከዚህ በኋላ "ኃላፊ" እየተባለ የሚጠራ እና አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

፳፫· የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

፩· ኃላፊው ከከተማው መስተዳድር በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት ጽሕፈት ቤቱን ይመራል ያስተዳድራል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ኃላፊው

*17. Drawing up Model Documents*

1) The notary may draw up model documents for those documents specified under Article 5 of this Proclamation and for such other documents as may be necessary;

2) Any person who desires to use a model document drawn up by the notary may get a copy thereof by paying the price prescribed by regulations issued pursuant to this Proclamation.

*18. Registration and Deposit of Documents*

1) The notary shall register all documents which he authenticates and deposits a copy for each document in his office;

2) Where the law provides for the deposit of a document with a notary, the notary shall register and deposit such document upon its submission;

3) Upon request by an interested person to get a copy of information about a document in the hands of the notary, the notary shall give the requested copy or information upon receipt of the appropriate charge.

PART 4

NOTARY OFFICES

**Section one**

*Regio Notary Offices*

*19. Organization*

1) To implement this proclamation Regional Administrations may organize notary offices.

2) They may issue details based on the facts of their respective area.

**Section two**

Addis Ababa and Dire Dawa notary offices ;

*20. Establishment of the Federal Notary Office*

1) Addis Ababa and Dire Dawa cities have notary office each.

2) The Federal Authenatication and Registrations Shall be Carried out by notary offices to be established in Addis Ababa and Dire Dawa cities.

*21. Powers and Duties of the Office*

The Office shall:-

1) Carry out the activities provided for under Article 4 of this Proclamation;

2) Draw up model documents pursuant to Article 17 of this Proclamation, as may be necessary;

3) enter into contract;

4) Own and transfer property;

5) carry out other activities necessary for the attainment of its purposes.

*22. Organization*

The Office shall have a head (hereinafter the "Head)" appointed by the City Governments and the necessary staff.

*23. Powers and Duties of the Head of the Office*

1) The Head shall direct and administer the Office in accordance with the general directives given by the City Government;

2) Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Head shall:–

ሀ) የከተማውን መስተዳድር እያስፈቀደ የጽሕፈት ቤቱን የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞችን በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጐች መሠረት ይቀጥራል ፣ ያስተዳድራል ፣ ያሰናብታል ፤

ለ) የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ለከተማው መስተዳድር አቅርቦ ያስጸድቃል ፤ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ሥራ ላይ ያውላል ፤

ሐ) የውስጥ ደንቦችንና መመሪያዎችን አዘጋጅቶ ለከተማው መስተዳድር ያቀርባል ፤ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል ፤

መ) ጽሕፈት ቤቱን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፤

ሠ) ስለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ክንውን ለከተማው መስተዳድር ምክር ቤት ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል ፤

ረ) በከተማው መስተዳድር የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል ።

፳፬· የጽሕፈት ቤቱ በጀት

የጽሕፈት ቤቱ በጀት፦

፩· ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ከሚሰበሰበው ገቢ ፣

፪· በከተማው መስተዳድር ከሚመደብለት የበጀት ድጐማና ፣

፫· ከሚያገኘው ስጦታና ዕርዳታ ፣ የተውጣጣ ይሆናል።

፳፭· የሒሣብ አያያዝና ምርመራ

፩· ጽሕፈት ቤቱ ተገቢውን የሒሳብ ሰነድ እና መዛግብት ይይዛል ፤

፪· የጽሕፈት ቤቱ ሂሳብ በየከተማው መስተዳድር ኦዲተር ይመረመራል ።

ክፍል ፭

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፮· ሰነድ የማረጋገጥ እና የመመዝገብ ሥልጣንና ተግባር ስለተሰጣቸው አንዳንድ የፌዴራል መንግሥት አካላት

፩· በውጭ አገር የኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ሰነዶችን ያረጋግጣሉ፤

፪· የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፤

ሀ) በኢትዮጵያ ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች እንዲሁም በኢትዮጵያ በሚገኙ የውጭ አገር ኤምባሲዎችና ቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የተረጋገጡ ሰነዶችን ፤

ለ) በተቀባዩ አገር ሕግ እንዲረጋገጡ የሚፈለጉ እና ወደ ውጭ የሚሄዱ ሰነዶችን ያረጋግጣል ።

፫· የመከላከያ ሠራዊት የክፍል ሹሞች በግዳጅ ላይ የሚገኙ የሠራዊቱ አባላት የሚያቀርቡላቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ፤

፬· የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኃላፊዎች እሥረኞች የሚያቀርቡላቸውን ሰነዶች ያረጋግጣሉ ፤

፭· በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት አካላት በዚህ አዋጅ ስለተሰጣቸው ሥልጣንና ተግባር አፈጻጸም እንደአስፈላጊነቱ መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ ።

፳፯· የተረጋገጡ ሰነዶች ሕጋዊ ውጤት

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት የተረጋገጠ ሰነድ በውስጡ ስለሚገኘው ይዘት ሙሉ እምነት የሚጣልበት በቂ ማስረጃ ነው።

፪· የተረጋገጠ ሰነድን መቃወም የሚቻለው ፍርድ ቤት በበቂ ምክንያት ሲፈቅድ ብቻ ነው ።

፳፰· ስለአገልግሎት ክፍያ

፩· ሰነድ አረጋጋጩ ለሚሰጠው አገልግሎት ተመጣጣኝ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል ።

፪· የክፍያው መጠን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፫ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል ።

(a) employ, administer and dismiss department heads of the Office and other employees in accordance with the Federal Civil Service Law with the approval of the City Government;

(b) submit the annual budget and work programme of the Office for approval to the City Government and implement the approved budget and work programme;

(c) prepare and submit internal regulations and directives to the City Government and implement the same after approval;

(d) represent the Office before third parties;

(e) submit to the City Government annual report concerning the performance of activities by the Office;

(f) carry out other related activities that may be assigned to him by the City Government.

*24. Budget of the Office*

The Budget of the Office shall be drawn from:–

1) revenue derived from the services rendered by it;
2) budget appropriation made by the City Government;
3) donations and assistance;

*25. Keeping of Accounts and Audit*

1) The Office shall keep books of account and record;
2) The Accounts of the Office shall be audited by the Auditor of the City Governments.

*PART 5*

*MSICELLANEOUS PROVISION*

*26. Notarial Powers and Duties Vested on Certain Institutions of the Federal Government*

1) Ethiopian Embassies and Consular Offices shall authenticate documents entering into Ethiopia.
2) The Ministry of Foreign Affairs shall authenticate:–
   (a) documents authenticated by Ethiopian embassies and consular offices and by embassies and consular offices of foreign countries in Ethiopia;
   b) Documents to be sent abroad that are required to be authenticated under the law of the receiving country.
3) Commanders of divisions of the defense force shall authenticate documents submitted by members of the defense force who are on active duty;
4) Heads of federal persons shall authenticate documents submitted by prisoners;
5) The heads of the institutions mentioned in this Article may issue directives of the implementation of the powers and duties given to them under this Proclamation.

*27. Legal Effect of Authenticated Documents*

1) A document authenticated in accordance with this Proclamation shall be conclusive evidence of its contents;
2) Authenticated documents may be challenged only with the permission of a court for good cause.

*28. Service Fee*

1) The notary may charge appropriate fees for his services;
2) The amount of service charge shall be determined by regulations issued under Article 33 of this Proclamation.

፳፱· <u>ስለቴምብር ቀረጥ ክፍያ</u>

ሰነድ አረጋጋጩ ሰነዱን አረጋግጦ ከመመዝገቡ በፊት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የቴምብር ቀረጥ መከፈሉን ማረጋገጥ አለበት ።

፴· <u>የተረጋገጠ ሰነድ ተቀባይነት</u>

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት በፌዴራል መንግሥት የሰነድ አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠ ሰነድ በክልል መንግሥታት ተቀባይነት ይኖረዋል ።

፪· እንደዚሁም በክልል ሰነድ አረጋጋጭ አካል የተረጋገጠ ሰነድ በፌዴራል መንግሥትና በሌሎች የክልል መንግሥታት ተቀባይነት ይኖረዋል ።

፴፩ <u>ከመደበኛ የሥራ ቦታ ውጭ አገልግሎት ስለመስጠት</u>

፩· ወደ ሰነድ አረጋጋጩ መደበኛ የሥራ ቦታ ለመሄድ የማይችል ሰው ሲጠይቅ ሰነድ አረጋጋጩ በጠያቂው አድራሻ በመገኘት የሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ይሰጣል ።

፪· እንደዚህ ላለው አገልግሎት ፣ ሰነድ አረጋጋጩ ተጨማሪ ክፍያ ሊጠይቅ ይችላል ።

፴፪· <u>ቅጣት</u>

በዚህ አዋጅ የተደነገገውን የተላለፈ ሰነድ አረጋጋጭ ወይም ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

፴፫· <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

የክልል መስተዳድሮች ፣ የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር ምክር ቤቶች ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ደንብ ሊያወጡ ይችላሉ ።

፴፬· <u>ተፈጻሚ የማይሆኑ ሕጎች</u>

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ፣ ደንብ ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

፴፭· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

*አዲስ አበባ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም·*

*ግርማ ወልደጊዮርጊስ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*
*ፕሬዚዳንት*

29. *Payment of Stamp Duty*

Before authenticating and registering a document the notary shall make sure that the stamp duty relating to the document is paid pursuant to the relevant law;

30. *Acceptance of Authenticated Documents*

1) Any document authenticated by a federal notary organ under this Proclamation shall be accepted by Regional Governments;
2) Similarly, any document authenticated by a Regional notary shall be accepted by the Federal Govoernment and other Regional Governments.

31. *Rendering Service Outside the Official Place of Work*

1) Where a person who is incapable of going to the official place of work of the notary request for his service, the notary shall render service of such person at the latter's address;
2) For the Service he renders under Sub-Article(1)of this Article the notary may charge additional fees.

32. *Penalty*

A notarry or any person who violates any of the provisions of this Proclamation shall be punished in accordance with the Penal Code.

33. *Authority to Issue Regulations*

Regional administrations, the City Government of Addis Ababa and the City Council of Dire Dawa may issue regulations for the implementation of this Proclamation.

34. *Inapplicable Laws*

No law, regulations, directives or customary practice, contrary to this Proclamation shall be applicable to matters provided for in this Proclamation.

35. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of 8th day of May, 2003.

*Done at Addis Ababa, this 8th day of May, 2003*

*GIRMA WOLDEGIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE